# በጀርመን የገባውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን በተመለከተ ያለው ቴክኒካዊና ተቋማዊ ልምድና አስተያየት - ክፍል 3

**ለተከበራቹህ ወገኖች** **07.04.2020**

## ኮረና ወረርሽኝን ለመከላከል ትኩረት የሚሹ ጎዳዮች

### 1. የህክምና መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ማሟላትና ምርመራ ማካሄድ

- በየአገሩ የታመሙ የኮሮና ህመምተኞች ቁጥር እየጨመረ ሲሆን በበሽታው ህይወታቸው የሚያልፈውም እንደዚሁ ከፍተኛ ነው። በየአገሩ የተወሰዱት እርምጃዎችም ውጤት እያሳዩ ነው፡፡ ሆኖም ሁኔታው አሁንም በጣም ውጥረት ላይ እና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። የጤና ሰራተኞች እና ከፍተኛ የፅኑ ህመምተኞች አልጋዎች ላይ እጥረት አለ። የህክምና ቴክኖሎጂም እና መሳሪያዎች ላይም ከፍተኛ እጥርት አለ። እዚህ ላይ በተለያዩ አገራት የተለያዩ የፈጠራ ዘዴዎችን በመጠቀም ችግሮችን ለመፍታት እየተሞከረ ነው። ከዚህ አንዱ 3-ዲ ማተሚያ (3-D Printer) ነው።
- 3-ዲ ማተሚያ (3-D Printer) ዋጋው ለግል መጠቀሚያ ከሚውለው 200 ዩሮ አንስቶ እስከ ፕሮፍሽናል የሆነው ከ3ሺ እስከ 9ሺ ዩሮ የሚደርስ ነው። ይህ ማተምያ የፕላስቲክ „ክሮችን“ በመጠቀም በማቅለጥ የተሰጠውን ቅርስ አትሞ የሚያወጣ ነው። በብዙ የቴክኒክ ማሰልጠኛዎች ተማሪዎች ይህንን ቴክኖሎጂ ለመማሪያ ይጠቀሙበታል። ይህ ለኢትዮጵያ ሊጠቅም የሚችል ሃሳብ ይመስለኛል። የተያያዘውን ምስል ይመልከቱ።
- በ3-ዲ ማተሚያ የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያ የተለያዩ ክፍሎችን በማተም አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ተችሏል። የመኪና አምራቾች እና ሌሎች ኩባንያዎችም ይህንን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያ የተለያዩ ክፍሎችን ለማምረት ጀምረዋል፡፡ በተጨማሪም የውሃ ዋና መጥለቂያ ማስኮች ላይ በ3-ዲ ማተሚያ (3-D Printer) ሞዲፋይ ሆኖ የተሰራ አካልን በመግጠም ወደ መተንፈሻ መሳሪያ መቀየር ተችሏል።
- ጀርመን ውስጥ አንድ የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያ (Mechanical Ventilator) ዋጋው ከ9ሺ እስከ 25ሺ ዩሮ ነው። የጀርመን መንግስት በቅርቡ 10ሺ የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያዎችን ገዝቷል። ስለዚህም ለአገራቸው በጣም ስለሚያስፈልግ እና እጥረትም ስላለ እንደዚህ ዓይነት እጅግ አስፈላጊ እቃዎች እንዳይወጡ እንደ ጀርመን በመሳሰሉት አገራት እገዳ በመደረጉ መሳሪያውን ለማግኘት እና በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን ለመርዳት አስቸጋሪ ነው። ቢቻልም እንኳ እቃው ታዞ የመጠበቂያ ጊዜው ርዝመት፣ ከዋጋ በመጠን ካለው ንፅፅር አኳያ የሚያስቸግር ነው። ህንድ በቅርቡ አንድ የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያ በ600 ዶላር ለማቅረብ እየሰራች መሆኑ የተዘገበ ሲሆን በቶሎ ማምረት ከተቻለና ወደ ለገበያ መቅረብ ከቻለ ችግሩን ለማቃለል ጠቃሚ እርምጃ ይሆናል ።

- የጀርመን የኮሮና መመርመሪያ አቅም በአሁኑ ጊዜ በሳምንት 360 ሺ ሲሆን ይህንን አቅም ለማሳደግ በትጋት እየተሰራ ነው፣ ኢትዮጵያም ውስጥ በአዲስ አበባ ሆነ በየክልሎቹ ተመጣጣኝ አቅም መፍጠር ያስፈልጋል።፡፡

- ይህም ሆኖ እያለ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች የሚኖሩበት አገር ከኢትዮጵያ በአንፃሩ ከፍተኛ የሆነ የበሽታው ተያዥ እና ሟች ያለበት ሲሆን በሚደርሰው የማህበርዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ጉዳት የሚደርስባቸው ከዚያም አልፎ በእጥረቱ ምክንያት የአፍንጫ እና የአፍ መከላከያ በቀላሉ ለማግኘት እንኳን ችግር ያለባቸው ቢሆንም የራሳቸውን ሁኔታ ሳያስቀድሙ ለኢትዮጵያ ከማሰብም አልፎ በቁስም ሆነ በገንዘብ ለመርዳት ብዙ ዝግጅቶችን እያደርጉ ይገኛሉ። ይህንን መንሳሳት ለምሳሌ እዚህ ከመቶ ሺ በላይ በወረርሽኙ በኤፊሻል በተያዙበት፣ ወረርሽኙ በየጎረቤቶቻችን እና በምናውቃቸው ባንኳኳበት ጀርመን የምንመለከትው ሲሆን በዚህም ኢትዮጵያዊያን ምን ያህል ለትውልድ አገራችው ልዩ ፍቅር እና እስከማውቀው ድርስ በሌሎች ዜጎች ላይ በማይታይ መልኩ ሲጨንቁ ማየቱ እጅግ የሚገርም ቁርኝት ከትውልድ አገራችው ኢትዮጵያ ጋር እንዳለቸው የሚያሳይ ነው። በዚህ ላይ መንግስትም ሆነ የተለያዩ ሜዲያዎች ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ከ"ዳያስፖራው" የተሰባሰቡ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፎች የሚደርሰውን አስከፊ ጉዳት ለመቀነስ በቶሎ አገር ቤት መድረስና ስራ ላይ መዋል አለባቸው። በተለያዩ ቡድኖች "gofundme" የተጀመሩ የገንዘብ ማሰባሰብ ሥራዎች ጥሩ ቢሆኑም ገንዘቡን በቶሎ ወደ አገር ቤት በማስተላለፍ መንግስት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በጅምላ እንዲገዙና በአጭር ጊዜ ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ማድረግ እንዲሁም በሽታውን ከመከላከል ጎን ለጎን ስራዎችና ድርጅቶች እንዳይዘጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶችን ለመቀነስ የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚገቡ ሴክተሮች፣ ፋብሪካዎች፣ ኢንቨስትመንቶችና አገልግሎቶች በጥናት ላይ ተመስርቶ ከመንግስት በቀጣይ በታክስ ቅነሳና ከወለድ ነጻ ብድርና በመሳሰሉት የድጎማ እርምጃዎች ሊዘረጉ ይገባል። በመጨረሻም በዚህ በሽታ የተያዙ እና በተለይም ህይወታቸውን ያጡት በአገር ቤትና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያኖች ሊታሰቡ ይገባል።


Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

## 2. የምግብና የፍጆታ እቃዎች አቅርቦት ሳይቋረጥ ማስቀጠል

- ጀርመን ውስጥ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስን የተከላከሉበት የመሰረታዊ ፍጆታዎች የአቅርቦት ስንሰለት አልተቋረጠም። ይህ ሁሉ ሲሆን በማንኛቸውም ዕቃዎች ላይ የዋጋ ጭማሪ አልተደረገም። ሱፐርማርኬት ሰው ሄዶ የዕለት ተዕለት ምግቡን ከመግዛት አላቋረጠም።
- ሰው እንዳይቀራረብ የሚያስገቡ እና የሚቆጣጠሩ ሰራተኞች በየቦታው ይገኛሉ። በአብዛኛው ሱፐርማርኬቱ ውስጥ ሻጮች በፕላስቶክ መስታዋት በተከለለ ቦታ ሲገኙ ደንበኛው የነካውን ቦታ በተለይም የካርድ መክፈያ ማሽኖችን ወዲያውኑ ያፀዳሉ። እዚህ ላይ ከጀርመን ልምድ በመነሳት ኢትዮጵያ ውስጥ ማይክሮፎኖች በስስ ፕላስቲክ እንዲሸፈኑ ባለፈው የሰጠሁት አስትያየት ተግባራዊ እንደሚሆን ተስፋ አልኝ።
- በዚህ አጋጣሚ ኢትዮጵያ እንደሰማሁት ጃንሜድ ላይ ለአትክልት ግብይት ጊዜያዊ ቦታ መፈቀዱ አጀማመሩ ጥሩ ነው። መሰረታዊ ፍጆታ በምንም አይነት መቋርጥ የለበትም።

## 3. የፈጠራና ምርምር ሥራዎችን በማበረታታት ወጪን መቀነስና ምርታማነትን ማሳደግ

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ባለፈው ባደርጉት ንግግር ላይ እንደጠቀሱት ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወጣቱ ለፈጠራ እና ለመመራመር ሥራዎች ትኩረት እንዲሰጥ አስቻኳይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መልካም ነው። ለምሳሌ በርካሽ ዋጋ የሚሰሩ የመተንፈሻ ማገገ መሳሪያዎች ማምረት የሚያስችልበትን ዘዴ መፈለጉ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ይህ ቪዲዮ ሊያስተምር ይችላል።

- የጀርመን መንግስት በወሰደው እርምጃ የህዝብ አስተያየት መመዘኛዎች እንድሚያሳዩት እስካሁን ከፍተኛ የሆነውን 95% ድጋፍ አግኝቷል። የጀርመን ኢኮኖሚ ከዚህ በፊት የነበሩ ቀውሶችን የተቋቋመው እና ውጤታማ የሆነው ከብድር ይልቅ በመቆጠብ ኢንቨስት ማድረግ ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ ስረዓት በመከተሉ፣ ቤተሰባዊ ይዘት ያላቸው የካምፓኒ ተከለ ቁመና፣ ፖዘቲቭ የመንግስት በጀት፣ እና በጥቂት ምርት ላይ ሳይሆን ጥራት ተኮር የሆኑ የተለያዩ የምርት ዓይነቶችን፣ ሚድልቄሮች እና የማምረቻ መሳሪያዎችን በማምረትና 40 ፐርሰንቱን ኤክስፖርት ማድረግ በመቻሉ ነው።

- ጀርመን በጤና ዘርፍም ውጤታማ የሆነው በሶሊደሪቲ ላይ ተመስርቶ ሁሉም ኢንሹራንስ የሚገባበት፣ ከደሞዙ በፐርሰንት የሚያዋጣበት እና ሰውም በነፃ የሚታከምበት የጤና ጥበቃ ስረዓት አንዱ ጠንካራ ምሶሶ ስለሆነ ነው። በዚህም ጀርመን የኮሮና ወረርሽኝን ለመመከትና በበሽታው ከተያዙት አንጻርና ከሌሎች አገራት ጋር ሲነጻጸር የሚቾች ቁጥር በጣም እንዲቀንስ ያገዘ ሲሆን በቀጣይም በፍጥነት ለማገገም ይረዳታል።

- በተጨማሪም ጀርመኖች ከፍተኛ የሀገር ፍቅር፣ መተባበር፣ ጠንካራ ዲስፕሊን፣ በኅፈታደኝነት፣ ለፈጠራ ትኩረት የመስጠት ባህሪያቸውና ውጤታም የሥራ ባህላቸው በቶሎ ከችግሩ ለመውጣት እንደሚረዳቸው ይታመናል። ጀርመኖች በአጭር ጊዜ ውስጥ 750 ቢሊየን ዩሮ ቢዝነሱ እንዳይሽመድመድ ለተለያዩ ድጎማዎች አዘጋጅተዋል። ኮሮናን ተዋጊ ጀግኖች የተባሉት በህክምናው ሴክተር ላሉ ባለሙያዎች፣ የሱፐር ማርኬት ሻጮች ወዘተ የደሞዝ ጭማሪ የሚያገኙበትን እየተነጋገሩ ነው። ለምሳሌ ሐምሌ ላይ የሰራተኛ ማህበሩ እና አሰሪው 1500 ዩሮ የአንድ ጊዜ ክፍያ ለህክምና ረዳቶች ከደሞዛቸው ጋር እንዲሰጣቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል። ሌላው ምሳሌ ደግሞ በትናንትናው ዕለት ጀርመን በኮሮና ቀውስ ምክንያት ለክስረት የተዳረጉ ተቋምት የሶስት ወር ገቢያቸውን ቢበዛ እስከ 800 ሺ ዩሮ ወለድ የለሽ ብድር መውሰድ ሲችሉ የብድር ዋስትናውን የጀርመን መንግስት እንደሚወስድ ተወስኗል።

- በጀርመን የመኪና ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ይገኛል። ፋብሪካዎች በመዘጋታቸው ምክንያት በማምረት ላይም ሆነ በማኔጅመንት ውስጥ የሚሰሩት በግዴታ እረፍት ወስደው እቤት እንዲቀመጡ፣ በሚቀጥሉት ጊዜያትም 60% ደሞዛቸውን እያገኙ እንዲቆዩ የተደረገ ሲሆን እንደየተቋሙ አቅምም ከዚህ በተጨማሪ ሌላ የማገገሚያ እርምጃ ሊኖር ይችላል። ይህም የመግዛት አቅምን በአጠቃላይ የሚያዳክም እና በዋጋ ፖሊስ ላይ ጫና የሚኖረው ይሆናል። 2% የሆነው የጀርመን ገበሬ ሙሉውን ጀርመን ከማብላት አልፎ ሌሎችን በሚረዳበት አቅሙ ላይ ችግር አጋጥሞታል። ይህም ከምስራቅ አውሮፓ ለሰብል አጨዳና የተለያዩ እገዛ ለማድረግ ወደ ጀርመን በየወቅቱ የሚመጡት 300 ሺህ


Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

ሰዎች የመቅረት ስጋት ነው። ቶሎ ሊበላሹ የሚችሉ አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች ላይ ችግር ሊፈጠርም ይችላል። እንደ መፍትሄ የተወሰደው በጎ ፈቃደኞችን ማነሳሳት፣ ስደተኞች (በስደት ላይ ሆነው ጉዳያቸውን የሚከታተሉትን) ማሰማራት ነው።

- ሌላው ምሳሌ ከጀርመን አልፈን ወደ ሆላንድ ስንሄድ በአበባ ንግዱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ነው የደረሰው። 60% ከስሯል። ከኬንያ እና ከኢትዮጵያ የሚመጡት ላይ ችግር በመፈጠሩ እና የአበባ ንግድ ፍላጎት በመቀንሱ በሆላንድ ከ150 ሺ በላይ የስራ ቦታ እና በአፍሪካ ወደ 1 ሚሊዩን የሚጠጋ የስራ ቦታ ስጋት ላይ ወድቋል። 50% የሚሆነው አበባም ተጥሏል። ይህም በሆላንድ በአበባ ገበያ በወር 1 ቢሊየን አበቦች ለግዢ ከሚቀርቡት ላይ ማለት ነው። በሳምንት እስከ 150 ሚሊዮን ዩሮ ክስረት እየደርሰበትም ነው። ይህም ያለ መንግስት ድጎማ መልሶ ማንሰራራት የሚችል አይመስልም።

## 4. የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን ማበረታታትና ትክክለኛ መረጃ ማቅረብ

- የጀርመን መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ በተጓጉሉ የሲቪል አስተዳደር ውስጥ ገብተው ሊረዱ የሚችሉበትን ዝግጁነት እና ዕቅድ የጀርመን መከላከያ ሚኒስተር በዛሬው ዕለት አቅርቧል።

- በተጨማሪም 90ሺ አባላት ያሉት የጀርመን የፌዴራል የበጎ ፈቃድ ግልጋሎት አባሎቹ በየትኛው መስክ፣ ቦት እና እንዴት እንደሚያገለግሉ የሚገልፅ የኢንተርኔት ፕላትፎርም አዘጋጅቷል።

- ሌላው ችግር እና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ስለ ኮሮና በየቀኑ ቁጥራቸው የሚበዛ ለማሳለጥ የማይሆኑ መርጃዎች አእምሮዋችንን እያጨናነቁ ይገኛል። የተጣሩ መረጃዎችን ከማግኘት ይልቅ የሚያሸብሩና የኮንስፐርሲ ዜናዎች እየተስፋፉ ይገኛል። በዚህም ምክንያት የጀርመን ፖሊስ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቁጥራቸው የበዛ ክሶችን እያስተናገደ ይገኛል። አንተርፖልም የኦንላይን ማርኬቲንግ አጭበርባሪዎችን በመከታተል ላይ ነው።

## 5. ከኮሮና ጉዳት በኋላ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማስፈጸሚያ ስልቶች መንደፍና መተግበር

- "ከኮሮና ጉዳት በኋላ" የሚል በጤና፣ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ ምን አይነት መንገድ መከተል እንደሚገባ የተለያዩ የጥናት ቡድኖች ስራቸውን ጀምረዋል። የኮሮና አስከፊ ገፅታ እንዳለ ሆኖ ከተፈጠረው ሁኔታ አንዳንድ ተስፋ የሚሰጡ ሁኔታዎች ይታያሉ። በከባቢ አየር ላይ መልካም ተፅእኖ መፈጠሩ፣ ከሚደርጉት ቁጥራቸው የበዛ ስብሰባዎች ከግማሽ በላይ የግድ አላስፈላጊ መሆናቸው መገንዘቡ፣ የቤት-ቢሮ የስራ ባህል፣ የኮሚዩኒኬሽን ዘዴዎች ሊሻሻሉ የሚችሉብትን መጠቆሚያ መፈጠሩ፣ ራስ ወዳድነትን መቀነሱ እና አንድነትን፣ የነዳጅ ቁጠባ፣ የመኪና እርጅና መቀነሻ፣ በሳይክል እና በእግር የሚደርጉ እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ ሁኔት የጨመረበት ወዘተ ነው። ኮሮናን ለማምከን ከተወሰደው እርምጃ ለመውጣት እና ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ ሰለሚተለመው ስትርቴጂ (exit stragety) በተመለከተ በሚቀጥለው ለማየት እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ሌሎች ተቋማት እና ታስክ ፎርሶች ለሚያደርጉት ከፍተኛ ጥርት ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከመልካም የጤናነት ሰላምታ ጋር

ፀጋዬ ደግነህ (ዶ/ር)

ዶ/ር ፀጋዬ ደግነህ ጉግሳ
በርሊን መጋቢት ፳፱ ፪ሺ፲፪ ዓ.ም. (*Berlin, 7th April, 2020*)



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh